
 

*በ"ብርሃን ለዓለም" ዓለም አቀፍ አገልግሎት የቀረበ፡*

# የ7ቱ ኮሎምቢያውያን ወጣቶች ራዕይ ስለ ገነት እና ሲዖል

www.DivineRevelations.info/AMHARIC

**እነዚህ 7 ኮሎምቢያውያን ወጣቶች በጋራ በኢየሱስ ክርስቶስ ተወስደው ገነትንና ሲዖልን አዩ። ይህ በገነት ስላዩት ድንቅ ውበት እና በሲዖል ስላዩት አሰቃቂ ነገር የሰጡት ምስክርነት ነው።**

*ይህ ትርጉም በመጣበት ቅጂ ምክንያት 6ቱን ምስክርነቶች ብቻ መዝግበናቸዋል።*

*በመጀመሪያ በስፓኒሽ ድምጽ ቅጂ የተገኘ ሲሆን ገለጻዎች/ስዕሎቹ የምስክርነቱ ክፍል ሳይሆኑ በኋላ ላይ የተጨመሩ ናቸው።*

# ስለ ሲዖል ራዕይ

# --- (1ኛ ምስክርነት) ---

(ሉቃስ 16:19) *ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር። ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ*

*አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።*

የእግዚአብሔር ቃል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሲዖልና ስለ ገነት በጣም ግልጽ ነው። ከላይ ባነበብነው ክፍል ውስጥ ጌታችን ስለ ሁለት ቦታዎች ይነግረናል፥ ስለ ሲዖልና ስለ ገነት፤ ስለመዳን አልያም ስለ መጥፋት በመካከል ሌላ ቦታ የለም። ፑርጋቶሪ(በካቶሊክ ትምህርት በሲዖልና በገነት መኻከል ያለ ቦታ ነው።) የሚባል የለም። ከእነዚህ ውጪ ሌላ ምንም አማካይ ቦታ እንደሌለ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስረዳናል።

(አፕሪል 11 በ1995ዓ.ም እ.ኤ.አ) እግዚአብሔር የህይወታችንን አቅጣጫ የሚያስቀየር ነገርን ገለጸለን። በዚህ ወቅት ገና ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ ማወቅ መጀመራችን ነበር። እኛ ይህንን ራዕይ ለአለም እንመሰክር ዘንድ ከእግዚአብሔር ልዩ መብትና ታላቅ ሀላፊነት የተሰጠን ሰባት ወጣቶች ነን።

ሁሉም ነገር የጀመረው ከጠዋቱ 4:00 ሠዓት አካባቢ ነው። በዚያን ዕለት ጸሎት አድርገን ወደ በኋላ ላይ ለመዝናናት እየተዘጋጀን ነበር። በድንገት ከጠዋቱ 4:00 ሠዓት አካባቢ ኃይለኛ ነጭ ብርሃን በመስኮት ገባ። ብርሃኑ እንደታየ ሁላችንም በልሳን መናገር ጀመርን፥ሁላችን በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቅን።

በጊዜው ሁላችንም ባየነው ነገር ተገርመንና ተደንቀን ነበር። ያ ታላቅ ብርሃን ክፍሉን ሁሉ አድምቆት ነበር። ብርሃኑም ከፀሐይ ብርሃን እጅግ የሚበልጥ ነበር። በብርሃኑም መኻከል ነጭ የለበሱ የመላእክትን ሠራዊት አየን። መላእክቱም እጅግ የሚያምሩ ረዣዥሞችና የተዋቡ ነበሩ።

በመላእክቱም መኻከል የሚያስደንቅ ነገር አየን -- የሰው ልጅ የሚመስለውን(የሰው ልጅ ምሳሌ)። ይህም ምሳሌ(አምሳያ) እጅግ የሚገርም ቁመና ነበረው፥ በጣም ነጭ የሆነ ልብስና መጎናጸፊያን የለበሰ ሰው። ጸጉሩም እነደ ወርቅ ፈትል ነበር። ከድምቀቱ የተነሳ ፊቱን ማየት አልተቻለንም። ነገር ግን በደረቱ ላይ እንዲህ የሚል ጽሑፍ በወርቅ የተጻፈበትን የወርቅ ቀበቶ አየን፦ *"የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ።"* በእግሩም ላይ የንጹህ ወርቅ ጫማን ተጫምቷል፥የእርሱንም ውበት የሚተካከለው የለም። የዚህን ሰው ግርማ ባየን ጊዜ ሁላችን በጉልበታችን ወደቅን።

ከዚያም ሁላችን ድምጹን መስማት ጀመርን። እጅግ የተለየና ድንቅ ነው፤ እያንዳንዱ ቃል፥በሁለት በኩል እንደተሳለ ሠይፍ ልባችንን ሰንጥቆ ገባ፤ ልክ በእግዚአብሔር ቃል እንደተጻፈው (ዕብራውያን 4:12)። በጣም ግልጽ፥ነገር ግን ኃያል በሆነ ቃላት ተናግሮናል። በግልጽም እንዲህ ሲል ሰምተነዋል "***የእኔ ታናናሽ ልጆች አትፍሩ፥እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ፤ በከተሞች፣ በሀገራት፣ በሕዝብም መካከል፤ በሁሉ ቦታ ትናገሩት ዘንድ ምስጢርን ላሳያችሁ ወደ እናንተ መጣሁ። ሂዱ ወደ እምላችሁ ቦታ ትሄዳላችሁ፥አትሂዱ ወደ እምላችሁ ቦታ ደግሞ አትሄዱም።"***

የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል (ኢዩኤል 2:28) "*ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጕበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ።"* ይኸ እግዚአብሔር ለሁሉ ያዘጋጀው ጊዜ ነው።

ከዚያም አንድ አስገራሚ ነገር ተፈጠረ፤ ድንገት በክፍሉ መኻከል አለት ታየ፤ ከእኛ ጋር የነበረው ጌታም፥ በአለቱ ላይ እንድንወጣ አደረገን። አለቱም ከመሬት ስምንት ኢንች ከፍታ ነበረው። ከዚያም በመሬት ላይ ትልቅ ጉድጓድ ታየ። ትልቅ ጥቁር አስፈሪ ጉድጓድ ወይም ዋሻ ነበር። ወዲያውም በአለቱ ላይ ሆነን በመሬት ውስጥ ወደ ጉድጓዱ ገባን። በጣም ጨለማ ነበር፤ ወደ ምድርም እንብርት ወሰደን።

*በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሳለን እጅግ ፈራን! እጅግ በጣም ስለፈራን ለጌታ እንዲህ አልነው "ጌታ ሆይ÷ ወደ እዚያ ቦታ መሔድ አንፈልግም! ወደ እዚያ ቦታ አትውሰደን ጌታ ሆይ! ከዚህ ቦታ አውጣን ጌታ ሆይ!"* ጌታም ደስ በሚልና በሚያረጋጋ ቃል መለሰልን÷ "*ለሌሎች ትነግሩ ዘንድ ይህን ልታዩ ለእናንተ ያስፈልጋችኋል።*"

*ቀንዳማ ቅርጽ ባለው ሸለቆ ውስጥ ነበርን፤ ከዚያም ጥላዎችን ማየት ጀመርን÷ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ሰይጣናትና አካላትን። ወደ ጥልቅ ዘልቀን መግባት ቀጠልን። በተወሰነ ቅጽበት ውስጥ ባዶነትና ፍርሀት እየተሰማን መጣ።*


*ከዚያም ወደ አንዳንድ ዋሻዎች፣ እንደ ሸለቆዎች አንዳንድ አስፈሪ በሮች። ወደ ውስጥ መግባት አልፈለግንም። አስጸያፊ ሽታንና የሚተናነቅ ሙቀትን አስተዋልን። በገባንም ጊዜ ዘግናኝ ነገሮችና አስፈሪ ምስሎችን አየን። ቦታው ሁሉ በእቶን የእሳት ነበልባሎች ተጥለቅልቋል፤ በእቶኖቹም(በእሳት ነበልባሎቹ) መኻከል በሺዎች የምቆጠሩ የሰዎች አካላት። በታላቅ መከራ እየተሰቃዩ ነበር። እጅግ አሰቃቂ ከመሆኑ የተነሳ የሚያሳየንን ነገር ለማየት አልፈለግንም።*

*ቦታው በተለያየ ስቃይና መከራ ስፍራዎች ተከፋፍሏል። ጌታ ሊያሳየን ከፈቀደው ከመጀመሪያዎቹ ክፍሎች አንዱ በእኛ አገላለጽ "የጋኖች ሸለቆ"* ("Valley of the Cauldrons") *ነው። በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ጋኖች ነበሩ። ጋኖቹም በመሬቱ ትክክል ተደርድረዋል፤ በእያንዳንዳቸውም ውስጥ የሚንቦገቦግ ፍም አለ። በእያንዳንዳቸውም ውስጥ ወደ ሲያል የወረዱ የሞቱ ሰዎች ነፍሳት አሉባቸው።*

*እነዚያም ሰዎች ጌታን ባዩበት ቅጽበት መጮህና ማልቀስ ጀመሩ "ጌታ ሆይ÷ ማረን! ጌታ ሆይ÷ ከዚህ ቦታ የምወጣበትን እድል ስጠኝ! ጌታ ሆይ÷ ከዚህ አውጣኝና ይህ ቦታ ለዓለም እውነት እንደሆነ እናገራለሁ!" ነገር ግን ጌታ ዞርም እንኳ ብሎ አላያቸውም። በዚያ ቦታ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም ወጣቶች ነበሩ። እንዲሁም ደግሞ ግብረ-ሰዶማውያንና ሰካራሞችንም ሲሰቃዩ አየን። እነዚህን ሁሉ ነፍሳት በስቃይ ብዛት ሲጮሁ አየናቸው።*

*ሰውነታቸው እንዴት እንደሚጠፋ ስናይ እጅግ ዘገነነን። ትሎች በባዶ የዓይኖቻቸው ቀዳዳ፣ በአፋቸው፣ በአፍንጫቸው ይገቡና ይወጡ ነበር፤ ቆዳቸውንም እየበሱ ወደ ውስጥ ሰውነታቸው ይገቡ ነበር። ይህም በእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ ነው።* (ኢሳይያስ 66፡24) "*ወጥተውም በእኔ ያመፁብኝን ሰዎች ሬሳቸውን ያያሉ፤ ትላቸው አይሞትምና÷እሳታቸውም አይጠፋምና፤ ለሥጋ ለባሽም ሁሉ አስጸያፊ ነገር ይሆናሉ።*" እንዲሁም (ማርቆስ 9፡44) "ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት"። በምናየው ነገር ሁሉ እጅግ ተረብሸን ነበር። ከ9 ጫማ(2.7 ሜትር) እስከ 12 ጫማ (3.6 ሜትር) ርዝመት ያላቸውን እቶኖችን(የእሳት ነበልባሎችን) አየን። በእቶኖቹም ውስጥ ወደ ሲያል የወረዱ የሞቱ ሰዎችን ነፍስ አየን።

*ጌታም ከጋኖቹ መካከል በአንደኛው ውስጥ ያለውን አንድ ሰው እንድናይ ፈቀደልን። ሰውየው ተዘቅዝቋል በፊቱም ላይ ያለው ሥጋ ይረግፍ ነበር። ጌታን በትኩረት ሲያይ ከቆየ በኋላ የጌታን ስም እየተጣራ ይጮህ ጀመር። እንዲህም ይል ነበር÷ "ጌታ ሆይ÷ ማረኝ! ጌታ ሆይ÷ እድል ስጠኝ! ጌታ ሆይ÷ ከዚህ ቦታ አውጣኝ!" ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ሊያየው እንኳን አልፈለገም። ጌታ ዝም ብሎ ጀርባውን ሰጠው። ኢየሱስም ይህንን ባደረገ ጊዜ ሰውየው ጌታን ይረግመውና ይሰድበው ጀመረ። ይህ ሰው ጆን ሌነን* (John Lennon) *የሰይጣናዊው የሙዚቃ ግሩፕ "ዘ-ቢትልስ"* ("The Beatles") *አባል ነበር። ጆን ሌነን በህይወት ዘመኑ በጌታ ሲቀልድና ሲያቃልለው የኖረ ሰው ነበር። ይህ ሰው ክርስትና ይጠፋል÷ክርስቶስም በሁሉ ይረሳል ብሎ ነበር። ሆኖም ግን÷ ይህ ሰው አሁን በሲያል ነው፤ ክርስቶስም ህያው ነው!! ክርስትናም አልጠፋም።*



በዚህም ስፍራ ጠርዙን ይዘን ስንሄድ ሳለ እነዚህ ነፍሳት እጃቸውን ወደ እኛ ዘርግተው ምህረትን ለመኑን። ኢየሱስንም ከዚህ ስፍራ እንዲያወጣቸው ጠየቁት፥እርሱ ግን በጭራሽ እንኳ አላያቸውም።

ከዚያም በሌላ ክፍል ውስጥ መሔድ ጀመርን። ከዛም እጅግ አስከፊው ስቃይ ወደሚደረግበት፥በጣም ዘግናኝ ወደ ሆነው የሲያል ክፍል ይህም ወደ ሲያል እንብርት ደረስን። እጅግ ጽኑ ስቃይ፥እንደዚህ ዓይነቱን ስቃይ የሰው ልጅ ሊገልጸው አይችልም። በዚህ ቦታ የነበሩት ብቸኛ ሰዎች ኢየሱስንና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቁ ሰዎች ናቸው። በዚህ ቦታ እረኞች (ካህናት፣ pastors) ፣ የወንጌል ሰባኪያን (evangelists)፣ መልዕክተኞች (missionaries) እና ሌሎችም ኢየሱስን ያወቁትና የተቀበሉት የእግዚአብሔርንም ቃል እውነቱን የሚያውቁ ነገር ግን ሁለት ዓይነት ህይወት የነበራቸው ናቸው።

እንዲሁም ወደ ቀደመ ግብራቸው (ኃጢአት፣ የዓለም ሀሳብ ...) የተመለሱም ይገኙባቸዋል፤ የእነዚህም መከራ ከሌሎቹ አንድ ሺህ እጥፍ ይከፋ ነበር። ይጮኹና ጌታን ምህረት ይለምኑት ነበር፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል (ወደ ዕብራውያን 10፡26-27) "*የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።*"

እነዚህ ነፍሳት በዚህ ስፍራ ሊገቡ የቻሉት፥ሰብከዋል፣ ጾመዋል፣ ዘምረዋል፣ በቤተ-ክርስቲያንም ውስጥ እጃቸውን ከፍ አድርገው ጸልየዋል፤ ነገር ግን በመንገድና በቤት ውስጥ ዘማዊ፣ ሌሰኛ፣ ውሸታምና ሌቦች ነበሩ፡ ፡እግዚአብሔርን ልንዋሽ አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ከተሰጠው ከእርሱ ብዙ ይጠበቃል ይላል። (ሉቃስ 12፡48)

ከዚያም ጌታ ሁለት ሴቶችን እንድናይ ፈቀደልን፥እነዚህ ሴቶች በምድር ሳሉ ክርስቲያን እህትማማቾች ነበሩ፤ ነገር ግን በጌታ ፊት በቅንነት አልተመላለሱም ነበር። አንዷም ለአንዷ እንዲህ ትላት ነበር "*አንቺ የተረገምሽ እርኩስ! እዚህ ቦታ መግባቴ ያንቺ ጥፋት ነው! ቅዱስ ወንጌልን አልሰበክሽልኝም! እውነቱንም ስላልነገርሽኝ አሁን እኔ በዚህ በሲኦል ነኝ!*" በእቶኑም ውስጥ ሆነው ይህን እርስ በእርሳቸው ይባባላሉ፥እናም ፈጽመው ይጠላላሉ፤ ምክንያቱም ፍቅር፣ ምህረት፣ ይቅርታ  በሲያል ውስጥ የለም።

የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቁ በሺሆች የሚቆጠሩ ነፍሳት ነበሩ፥ነገር ግን በጌታ ፊት በንጽህና አልተመላለሱም ነበር። "***በእግዚአብሔር አንዲሁም በሲያል እቶን መቀለደ አትችሉም***" አለን ጌታ። እንደገናም "***ልጆቼ፥በምድር ላይ ያለው መከራ ሁሉ በአንድ ቦታ ቢከማች ምንም ማለት አይደለም፥በሲያል በተሻለው ስፍራ አንድ ሰው ከሚሰቃየው ጋር ሲነፃጸር ምንም ማለት አይደለም።***" በትንሹ ለሚሰቃዩት ያን ያህል ከባድ ከሆነ የጌታን ቃል ላወቁት ነገር ግን ከፈቃዱ ውጭ ለተመላለሱት በሲያል እንብርት ላሉት ምን ያህል ይከብድ። ከዚያም ጌታ ለእኛ በእሳት ለምንጫወተው በምድር በእሳት መጫወት እንደምንችል በሲያል ግን በጭራሽ በእሳት መጫወት እንደማንችል ነገረን።

በተለያዩ ቦታዎች መሔድ ቀጠልን እናም ጌታ ብዙ ሰዎችን አሳየን። በዚያ ያሉ ሰዎች ወደ ስድስት የሚጠጉ የተለያዩ ስቃዮችን እንደተቀበሉ ማየት እንችላለን። በሁሉም ዓይነት ስቃዮች በሰይጣን የሚሰቃዩ ነፍሳት ነበሩ። ሌላኛው ከባዱ ስቃይ ደግሞ ህሊናቸው የሚወቅሳቸው ነው "*አስታውስ ሲሰብኩልህ፣ አስታውስ የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰማ፣ ስለሲያል ሲነግሩህ እንደሳቅህ!*" የገዛ ህሊናቸው ያሰቃያቸዋል፥ልክ ሙሉ ሰውነታቸውን እንደሚያቆራርጡት ትሎች፥ልክ እኛ ከምናውቀው ሺህ ጊዜ ሺህ እጥፍ እንደሚበልጠው እንደሚፋጀው እሳት። ይህ ሰይጣን ለሚፈልጉትና ለሚከተሉት ሁሉ ያዘጋጀው ሽልማት ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል (ራዕይ 21፡8) "*ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።*"

ቀጥሎም ጌታ ስድስት ሰዎችን የገደለን ሰው አሳየን። እነዚህም ስድስት ሰዎች ዙሪያውን  ከበው እንዲህ እያሉ ይጮኹበት ነበር "*ሁላችንም በዚህ ስፍራ ያለነው በአንተ ጥፋት ነው፥በአንተ ጥፋት!*" ገዳዩም ጆሮውን

በእጆቹ ለመሸፈን ይሞክራል ነገር ግን አይቻለውም፥ምክንያቱም በሲዖል ሁሉም የስሜት ህዋሳቶቻችን አብዝተው ይሰማሉና ነው።



በዚያ ስፍራ ያሉ ነፍሳት ሊቋቋሙት በማይችሉት በማንኛውም መንገድ ሊያረኩት በማይቻል የውኃ ጥም ይሰቃያሉ፥ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳለው የዓላዛርና የሀብታሙ ሰው ታሪክ። (ሉቃስ 16፥19) ሀብታሙ ሰው በሲዖል ሆኖ ጠብታ ውኃ ይናፍቅ ነበር፥ ያ ብቻ ይበቃዋል። የጌታ ቃል እንዲህ ይላል (ኢሳይያስ 34፡9) "*የኤዶምያስም ፈሳሾች ዝፍት ሆነው ይለወጣሉ፥ አፈርዋም ዲን ይሆናል፥መሬትዋም የሚቃጠል ዝፍት ትሆናለች።*"

በዚያ ቦታ ሁሉም ነፍሳት በእሳት ውስጥ ናቸው። ሰዎች የወንዝን ነጸብራቅ ያያሉ፥ለመጠጣት በሞከሩ ጊዜ ግን ወደ እሳትነት ይለወጥባቸዋል። እንዲሁም በወኖች የለመለሙ ዛፎች አፍርተው ያያሉ፥ፍሬውን ለመውሰድ በሞከሩ ጊዜ ግን እጃቸውን ያቃጥላቸዋል፤ ሰይጣኖችም እነዲህ እያደረጉ ያሾፉባቸዋል።

ከዚያም ጌታ እስካሁን ካየናቸው ቦታዎች ወደ ከፋ ቦታ ወሰደን። ከዚያም የእሳትን ሐይቅና ድኝ አየን። በእሳቱም ሌላኛው ዳር አነስተኛ ሐይቅን አየን። በዚያች አነስተኛ ሐይቅ ውስጥ ሚሊየኖችና ሚሊየኖች ሚሊየን ነፍሳት እንዲምራቸው ወደ ጌታ ይጮኹና ያለቅሱ ነበር። እንዲህም ይሉ ነበር "*እባክህ ጌታ ሆይ! ቢያንስ ለጥቂት ቆይታ እንኳን ከዚህ አውጣን! እባክህን የመውጣትን እድል ስጠኝ!!!*" ነገር ግን ጌታ ምንም ሊያደርግ አልቻለም አንድ ጊዜ ተፈርዶባቸዋልና።

ከነዚያ ሁሉ ሚሊየን ሚሊየን ሰዎች ውስጥ ጌታ ከወገብ በታች በእሳቱ ሐይቅ ውስጥ ወደ ሰመጠ አንድ ሰው እንድናተኩር አደረገን። ጌታም የዚህን ሰው ሀሳቡንና እውቀቱን እነድንረዳ አደረገን። የዚያም ሰው ስም ማርክ ይባል ነበር። ከዚያም ሰው አስተሳሰብ ይህንን ዘላለማዊ ትምህርትን አገኘን "*በእናንተ ቦታ ለመሆን ማንኛውንም ነገር እሰጣለሁ! ወደ ምድር ለአንድ ደቂቃ እንኳን ለመመለስ ማንኛውንም ነገር እሰጣለሁ! ህይወቴ እጅግ የተመሰቃቀለ ቢሆን፣ እጅግም በሽተኛ ብሆን፣ በዓለምም የተጠላሁ ብሆን ምንም አይገደኝም፥ ወደ ምድር ለመመለስ ማንኛውንም ነገር እሰጣለሁ! በምድር ላይ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ቢሆን።*" ጌታ ኢየሱስ እጄን ይዞት ነበር። ኢየሱስም ለማርክ አስተሳሰብ እንዲህ ሲል መለሰለት "***ማርክ፥ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ወደ ምድር ለመመለስ ለምን ፈለግህ?***" በስቃይና በሰቆቃ ድምጽ እንዲህ ሲል ለኢየሱስ መለሰለት "*ጌታ ሆይ፥ለአንድ ደቂቃ እንኳን ወደ ምድር ለመመለስ የምፈልገው ንሰሐ ለመግባትና ለመዳን ነው።*"

ጌታም ማርክ ያለውን በሰማ ጊዜ፥ ደም ከቁስሎቹ ሁሉ ፈሰሰ ዓይኑም በእንባ ተሞላ፤ እንዲህም አለው "***ማርክ፥ ጊዜው ለአንተ በጣም ረፍዷል! ለመኝታህ ትሎች ተዘጋጅተዋል ትሎችም ይሸፍኑሀል***" (ኢሳይያስ 14፡11) ጌታም ይህን በተናገረው ጊዜ ለዘላለም ወደ ሐይቁ ሰመጠ። በሚያሳዝን ሁኔታ በእዚያ ላሉ ነፍሳት ምንም ተስፋ የላቸውም። ነገር ግን በዚህ ምድር ላለነው ለእኛ ብቻ አሁን ንሰሐ በመግባት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ገነት የመሔድ እድል አለን።

አሁን ደግሞ ይህን ምስክርነት እንድትሰጥ ከእህቴ ጋር እተዋችኋለሁ። አመሰግናለው።

---

# --- (2ኛ ምስክርነት÷ሉፒ) ---

**የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እስኪ የእግዚአብሔርን ቃል እናንብብ (መዝ.18:9) “*ሰማዮችን ዝቅ ዝቅ አደረገ ወረደም÷ጨለማ ከእግሩ በታች ነበረ።*” ጌታም እጄን ዘረጋልኝና እጄን ያስኩት÷ ተያይዘንም በዋሻው ውስጥ ቁልቁል መውረድ ጀመርን። ዋሻው የጌታን እጅ ያልያዝኩበትን ሌላኛውን እጄን ማየት እስኪያቅተኝ ድረስ እየጨለመ እየጨለመ መጣ።**



**በድንገት በጣም ጥቁር አንጸባራቂ ድምጽ የሚሰጥን ነገር አለፍን። ጨለማው በጣም ድቅድቅ ያለ ከመሆኑ የተነሳ እጃችሁ የዋሻውን ግድግዳ ለማግኘት አይችልም። ጉዞአችን በጣም ፈጣን ከመሆኑ የተነሳ ነፍሴ ከሰውነቴ የተለየች ያህል ተሰማኝ።**

**ወዲያውም የበሰበሰ ሥጋ ዓይነት ሽታ ሸተተኝ። ሽታውም በእያንዳንዱ ቅጽበት እየከፋ ይሔዳል። ከዚያም የሚሊየኖችና ሚሊየኖች ነፍሳትን ጩኸት ሰማሁ። ያለማቋረጥ ይጮኹ÷ ያለቅሱና የሲቃን ድምጽ ያሰሙ ነበር። በጣም ከመፍራቴ የተነሳ ወደ ጌታ ዞሬ እንዲህ አልኩት፦ “*ጌታ ሆይ÷ ወዴት ነው የምትወስደኝ? ጌታ ሆይ÷ እባክህ ማረኝ! ጌታ ሆይ÷ እባክህ ማረኝ!*” ጌታ ይህን ብቻ ነበር የተናገረኝ “*ለሰው ሁሉ እንድትናገሪ ይህንን ማየት ያስፈልግሻል።*”**

**ፈጽሞ ጨለማ ወደሆነ ቦታ እስክንደርስ ድረስ በዚህ ቀንድ በሚመስለው ዋሻ ውስጥ መሔድ ቀጠልን። ከዓይኔ ላይ ከባድ መጋረጃ እንደመግለጥ ዓይነት ሚሊየኖችና ሚሊየኖች እቶኖችን አየሁ። ከዚያም የከፋ÷ ብዙ አሰቃቂ ጩኸቶችን ሰማሁ ነገር ግን ማንንም ማየት አልቻልኹም። በጣም ፈርቼ ነበር። ለጌታ እንዲህ አልኩት “*ኦ ጌታ ሆይ÷ እባክህ ማረኝ! ኦ ጌታ ሆይ÷ እባክህ ማረኝ! ወደ እዚህ ቦታ አትውሰደኝ! ይቅር በለኝ!*” በዚህ ሠዓት በሲያል ታዛቢ መሆኔን አላሰብኹም÷ የፍርድ ቀን ነው የመሰለኝ። በጌታ ኢየሱስ ፊት ቆሜ በኃይል እየተንቀጠቀጥሁ ነበር÷የእውነት ይህ የህይወቴ መጨረሻ ነበር የመሰለኝ።**

**ከፊታችን ወዳለ ትልቅ እቶን ቀረብን÷ ግዙፍና ባስፈሪ ሁኔታ የሚነድ ነበር። ብዙ እቶኖችን እያየሁና ሚሊየኖች ነፍሳት በአንድ ድምጽ ሲያለቅሱ እየሰማሁ በቀስታ ወደ እታች መጓዝ ቀጠልሁ። ከዚያም እሳት ያልበላው የእንጨት ጠረጴዛ አየሁ። የቢራ ጠርሙሶች የሚመስሉ በላዩ ላይ አሉት። የሚያረካ ይመስላል ነገር ግን በውስጡ እሳት ሞልቶበታል። ይህን እያየሁ ሳለ ድንገት አንድ ሰው መጣ። ሥጋው ሙሉ በሙሉ አልቋል ማለት ይቻላል÷ ከልብሱም የተረፈው የጨቀየና እየተቃጠለ ነበር። ከእሳቱ የተነሳ አይኖቹን ሁሉ፣ አፉንም ጸጉሩንም አቷል። አይን ባይኖረውም ግን ያየኝ ነበር። እላችኋለሁ ይህ በትክክል የሚያስብ፣ የሚያሰላስል በትክክል የሚያይ ሰው ነፍስ እንጂ የተፈጥሮ ሰውነት አይደለም።**



**ሰውዬውም የሰለለ እጁን ወደ ጌታ ዘርግቶ እንዲህ እያለ ያለቅስ ጀመር “*ጌታ ሆይ÷ ማረኝ! ጌታ ሆይ÷ ማረኝ! እየተሰቃየሁ ነው! እየተቃጠልኩ ነው! እባክህ ማረኝና ከዚህ ቦታ አውጣኝ!*” ጌታም በርህራሄ ተመለከተው ከዚያም እጄን የሆነ ሞቅታ ተሰማኝ።**
**አየሁም ደም ነበር ... የኢየሱስ ደም! ይህን የሚሰቃይ ሰው በእቶኑ ሲዋጥ እያየ የጌታ ደም ከእጁ ይወጣ ነበር።**

ሰውየው ትኩረቱን ወደ ጠረጴዛው አድርጎ ወደ ጠርሙሶቹ ሔደ። ነገር ግን ጠርሙሱን አንስቶ ሊጠጣ ሲል እሳትና ጭስ ከጠርሙሱ ውስጥ ተመንጥቆ ወጣ። ጭንቅላቱን ወደ ኋላ መለሰና ሰምቼው የማላውቀው ዓይነት ጩኸት ጮኸ። በታላቅ ህማምና ሰቆቃ ካለቀሰ በኋላ በጠርሙሱ ውስጥ ያለውን መጠጣት ጀመረ። ነገር ግን ጠርሙሱ በአሲድ የተሞላ ነበረና ጉሮሮው ሙሉ በሙሉ ወደመ። አሲዱ በሆዱ ውስጥ ሲያልፍ ሲጎዳው ታያለችሁ።

በዚህ ሰው ግንባር ላይ 666 የሚለው ቁጥር ታትሞበት ነበር። በደረቱ ላይ በሙቀቱም ሆነ በትሎቹ እንኳን ሊጠፋ የማይችል ባልታወቀ ብረት የተሠራ ሰህን አለ። በላዩም እኛ ልንረዳው የማንችለው ጽሑፍ አለ። ጌታ በምህረቱ ትርጓሜውን ገለጸለን። "***ወደ እዚህ ቦታ የመጣሁት ሰካራም ስለሆንኩ ነው።*** " ጌታን ምህረትን ለመነው፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ይነግረናል (1ቆሮ.6:10) "*ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።*"

ጌታም የዚህን ሰው በምድር ላይ የነበረውን የመጨረሻውን ህይወቱን እንደ ፊልም አሳየኝ። የዚህን ሰው ከመሞቱ በፊት የመጨረሻው ሰከንድ ልክ በቴሌቪዥን እስከሪን ዓይነት አሳየኝ። የዚህ ሰው ስም ሉዊስ ይባል ነበር እና በመጠጥ ቤት እየጠጣ ነበር። በመጠጥ ቤቱ ውስጥ የነበረውን ዓይነት ጠረጴዛና ጠርሙስ አየሁ። በጠረጴዛውም ዙሪያ ጓደኞቹ ነበሩ። (*አሁን አንድ ነገር ልንገራችሁ፥ **አንድ** ብቻ **እውነተኛ ጓደኛ** አለ፥ ስሙም **ኢየሱስ ክርስቶስ** ነው፡ ታማኝ ጓደኛ እርሱ ብቻ ነው።*) ሉዊስ እየጠጣ ነበር ጓደኞቹ ግን ቀድሞዉንም ሰክረው ነበር። የቅርብ ጓደኛው ጠርሙስ አነሳና ሰበረው ከዚያም ሉዊስን መውጋት ጀመረ። ሉዊስንም በመሬት ላይ ሲያየው ጥሎት እየሮጠ ጠፋ፤ ሉዊስም እስኪሞት ድረስ ደም ፈሰሰው። የሚያሳዝነው ነገር ያለ ክርስቶስ መሞቱ ነው።

በዚሁሉ ነገር መሀል፥ እነዚያ ሁሉ ነፍሳት እያለቀሱ፥ ጌታን አንድ ነገር ጠየቅሁት "*ኦ ጌታ ሆይ፥ ይህ ሰው ስለአንተ ያውቅ ነበር? ስለ ድነትስ ያውቅ ነበር?*" ጌታም እያዘነ መለሰልኝ "***አዎን ሉፒ፥ የግል አዳኙም አድርጎ ተቀብሎኝ ነበር። ነገር ግን አላገለገለኝም።***" ከዛም የበለጠ ፍርሀት ተሰማኝ። ሉዊስ በኃይል እያለቀሰ ጮኸ "*ጌታ ሆይ፥ እጅግ ያማል! እጅግ ያማል! እባክህ ማረኝ!*" እጁንም ወደ ጌታ በድጋሚ ዘረጋ፤ ነገር ግን ጌታ የእኔን እጅ ያዘና ከእቶኑ ርቀን ሔድን። ሉዊስን እየዋጡት ያሉት እቶኖች እያየሉና እየጨመሩ መጡ "*ማረኝ! ማረኝ!*" ከዚያም በእቶኑ ውስጥ ተሰወረ።

ጉዟችንን ቀጠልን፥ ይህ ቦታ ግዙፍና የሚያስፈራ ነበር! ሌላ እቶን ጋር ስንደርስ ጌታን እንደዚህ አልሁት "*ጌታ ሆይ፥ በቃ! እባክህን ከዚህ በኋላ ይህን ቦታ ማየት አልፈልግም! ይቅር እንድትለኝ እለምንሀለሁ! እባክህ ይቅር በለኝ! ይህን ማየት አልፈልግም!*" ስለዚህ ዓይኔን ጨፈንሁ ነገር ግን ለውጥ አልነበረውም ዓይኔን ጨፍኜም ገልጬም ሁሉም ነገር ይታየኛል። ይህ እቶን ቀስ እያለ እየቀነሰ መጣና አንዲት ሴት አየሁ። በጭቃ ተሸፍና ነበር፤ ጭቃው ደግሞ በትሎች ተሞልቷል። በጣም ጥቂት ጸጉር ነበራት፥ እናም ትሎች በወረሩት ጭቃ ተለውሳለች። ሙሉ በሙሉ በትሎች ተወርሳ ትጮሃለች "*ጌታ ሆይ፥ ማረኝ! ጌታ ሆይ፥ እዘንልኝና ይቅር በለኝ! ተመልከተኝ! ያማል! ማረኝ! እነዚህን ትሎች አስወግድልኝ! ከዚህ ስቃይ አውጣኝ በጣም ያማልና!*" ጌታ በታላቅ ሐዘን ዝም ብሎ ያያት ነበር። እጁን በያዝነው ጊዜ በሲዖል ውስጥ ለዘላለም በእቶን ስለሚቃጠሉት ነፍሳት የልቡ ህማምና ስቃይ ይሰማናል።

ይህች ሴት ዓይንም ሆነ ከንፈር የላትም፥ ነገር ግን ታያለች ይሰማታልም፤ ህማሙ ሁሉ እንዲሁ ይጠነክራል። በእጇ በአሲድ የተሞላ ጠርሙስ አለ፥ ነገር ግን ሽቶ እንደሆነ ታምናለች። ለእኔ አሲድ እንደሆነ ይታየኛል፥ ሰውነቷን በተረጨችው ጊዜ ሁሉ ያቃጥላታል። ቢሆንም ግን እየደጋገመች አሲዱን በሰውነቷ ላይ ትጨምራለች። በተደጋጋሚ ውድ ሽቶ እንደ ሆነ ትናገራለች። በተጨማሪም ደግሞ የሚያምር የአንገት ሀብል እንዳጠለቀች ታምናለች፥ ለእኔ ግን የሚታየኝ በአንገቷ ዙሪያ የተጠመጠሙ እባቦችን ነው። በጣም ውድ የሆነ የእጅ አምባርም እንዳደረገች ታምናለች፥ ነገር ግን እኔ ትሎች እንደሆኑ ይታየኛል፥ ወደ አንድ ጫማ ርዝመት ሲኖራቸው በቁጣም አጥንቷን ይሰረስሩ ነበር። ያሏት ጌጦቿ ብቻ እንደሆኑ ብትናገርም እኔ ግን ጊንጦችና ትሎች መላ ሰውነቷን ወረዋት አየሁ። በሲዖል ያሉት ሁሉ ያላቸው የብረት ሳህን ነበራት። እንዲህም ይላል "***እዚህ ያለሁት በስርቆት ነው።***"

*ይህች ሴት ስለ ኃጥያቷ ምንም አትጸጸትም። ጌታም ጠየቃት "**መግደሊና፥ እዚህ ቦታ የመጣሽው በምን ምክንያት ነው?**" እርሷም መለሰች "ሌሎችን ስሰርቅ ምንም አይገደኝም ነበር፤ ሁሌም የምጨነቀው ስለ ጌጦቼና ውድ ሽቶ ስለማግኘት ነው፤ ማንንም ልስረቅ እስካማረብኝ ድረስ አይገደኝም።"*

*ትሎቹ ሁሉ ሰውነቷን ሲሸነቁሩ እያየሁ የጌታን እጅ ያዝሁ። መግደሊና የሆነ ነገር እየፈለገች ፊቷን አዞረች። አሁንም ጌታን ጠየቅሁት "ይህች ሴት ስለ አንተ ታውቅ ነበር? " ጌታም መለሰለኝ "**አዎ፥ ይህች ሴት ታውቀኝ ነበር።**"*

*መግደሊና እንዲህ እያለች ዙሪያዋን መፈለግ ጀመረች "ጌታ ሆይ፥ያቺ ስለ አንተ ስትነግረኝ የነበረችው ሴት የታለች! የታለች! ሲዖል ውስጥ ለ15 ዓመታት አለሁ።" ሁሉም በሲያል ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉንም ነገር ያስታውሳሉ። መግደሊና መጠየቋን ቀጠለች "የታለች ይህች ሴት? አትታየኝም!" ሥጋዋ በአንድ ቦታ ስለ ነበረ ሰውነቷ እንደማይዟዟር አወቅሁ። ያቺን ስለ እግዚአብሔር የነገረቻትን ሴት ለማግኘት ወደ ሌሎቹ እቶኖች እየዞረች ለማየት ሞከረች። ጌታም መለሰ "**አይ! አይ መግደሊና እዚህ የለችም ፥ስለ እኔ ስትነግርሽ የነበረችው ሴት ከእኔ ጋር በመንግሥተ ሰማያት ናት።**"*

*ይህን ስትሰማ እራሷን ወደ እቶኑ ወረወረች፥የባሰም አቃጠላት። የብረት ሰሀኗም እንደሌባ ፈረደባት። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንድታነቡ እፈልጋለሁ (ኢ.ሳ.3:24) "እንዲህም ይሆናል፤ በሽቱ ፋንታ ግማት፥ በመታጠቂያውም ፋንታ ገመድ፥ጠጕርንም በመንቀስ ፋንታ ቡሀነት፥በመጐናጸፊያ ፋንታ ማቅ፥በውበትም ፋንታ ጠባሳ ይሆናል።"*

*ከጌታ ጋር ጉዟችንን ስንቀጥል፥በትሎች የተሞላን ረድፍ አየሁ። በዙሪያውም በቀይ የጋለ ብረት የተሠራ ተንሸራታች አለ። በዚህም ረድፍ ከማንኛውም አቅጣጫ የሚታይ በድምቀት የሚያበራ የማስታወቂያ ሰሌዳ አለ። እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለበት "**ሁላችሁ ውሸታሞች እና ሀሜተኞች እንኳን ደህና መጣችሁ።**" በተንሸራታቹም መጨረሻ ትንሽ የሚፈላ መስኖ አለ። የሚነድ ድኝን ይመስላል። ከዚያም ሙሉ ለሙሉ እራቁቱን የሆነ ሰው በመንሸራተቻው ሲወርድ አየሁት። ሲንሸራተቱ ቆዳቸው እየተላጠ መንሸራተቻው ላይ ይለጠፍ ነበር። በሚነድደው መስኖ ውስጥ በወደቁ ጊዜ ምላሳቸው እስኪፈነዳ ድረስ ያብጥና በምላሳቸው ፋንታ ትሎች ይወጡ ነበር። ይህ፥ስቃያቸውን ይጀምረዋል። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል (መዝ.73:18) "በድጥ ስፍራ አስቀመጥኻቸው፥ወደ ጥፋትም ጣልኻቸው። እንዴት ለጥፋት ሆኑ! በድንገት አለቁ ስለ ኃጢአታቸውም ጠፉ።"*

*እነዚህን ካየን በኋላ ከሲያል ተመለስን። ልነግራችሁ የምፈልገው ሲያልና ገነት አሁን ከምናውቀው አካላዊ ዓለም የበለጠ እውነተኛ እንደሆኑ ነው። ወዴት አቅጣጫ መሔድ እንዳለባችሁ የምትወስኑት እዚህ ነው፤ ወደ ለዘላለማዊ ከክርስቶስ ጋር ማሳለፍ አልያም ወደ ሲዓል እሳት። ጌታ እየደጋገመ እንዲህ ይለናል "**ያለ ቅድስና ማንም ሰው አያየኝም፥ያለ ቅድስና ማንም ሰው አያየኝም።**" (ዕብራውያን 12:14) ስለዚህ ነው አሁንም እኔ ይህንኑ ነገር የምነግራችሁ "**ያለ ቅድስና ጌታን ልታዩት አትችሉም።**"*

---

# --- (3ኛ ምስክርነት፥ ሳንድራ) ---

እስቲ የእግዚአብሔርን ቃል እንይ (ማቴዎስ 10:28) “*ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።*”



የሰው ነፍስ ወደ ሲኦል በመጣች ጊዜ የሞትን ሰውነት ይዋሀዳል። ጌታ ኢየሱስም እጄን ይዞኝ እጅግ ጥልቅ በሆነ ጨለማ ዋሻ ውስጥ ቁልቁል ወደ ምድር እንብርት መሔድ ጀመርን። ብዙ በሮችም ወዳሉት ስፍራ ደረስን፤ አንደኛውም ተከፈተና ከጌታ ጋር ወደ ውስጥ ገባን። የጌታን እጅ በፍጹም አልለቀቅሁም፥ ምክንያቱም ከለቀቅሁት ለዘላለም በሲኦል እነደምቀር ስለገባኝ ነው።

በበሩ እየገባን ሳለ ግዙፍ ግድግዳን አይቼ ነበር። በጭንቅላታቸው በመንጠቆ የተንጠለጠሉ ብዙ ሺህ ሰዎች ነበሩ፥ እጃቸውም በእግር-ብረት ከግድግዳው ጋር ተጠፍሯል። እንዲሁም ብዙ ሺህ ነፍሳትን በእቶኖች መኻከል በየቦታው ቆመው አየን።

ከዚያም ወደ አንዱ እቶን ፊት ቀስ እያልን መውረድ ጀመርን። ወዲያውም በእቶኑ ውስጥ የሆነ ሰው አየሁ፥ ከንግግሩ ወንድ እንደሆነ አወቅሁ። ሰውየው የካህን ልብስ ለብሶ ነበር፥ ልብሱም ሙሉ በሙሉ አስቀያሚና የተቦጫጨቀ ነበር። ትሎች በዚህ ሰውዬ ሰውነት ወደ ውጪና ወደ ውስጥ ይርመሰመሱ ነበር። በእሳት የከሰለና ያረረ ይመስላል። ዓይኑ ተጠንቁሎ የወጣና ሥጋውም ከላዩ ላይ እየቀለጠ ወደ መሬት ይወድቅ ነበር። ነገር ግን ሁሉም ሥጋው ረግፎ ካለቀ በኋላ እንደ ገና ያድግና የቀደመው ሂደት ይቀጥላል።

ኢየሱስን ባየው ጊዜ እንዲህ አለው “*ጌታ ሆይ፥እዘንልኝ፥እዘንልኝ! እባክህ ለአንድ አፍታ እንኳን ከዚህ ቦታ አውጣኝ! ለአንድ ደቂቃ እንኳን!*” በሰውየው ደረት ላይ የብረት ሳህን ነበር እንዲህም ይላል “***እዚህ ቦታ ያለሁት በስርቆት ነው።***”

ኢየሱስም ተጠግቶ ሰውየውን ጠየቀው “***ስምህ ማን ነው?***” ሰውየውም መለሰ “*አንድሪው፥ስሜ አንድሪው ነው ጌታ ሆይ*” ጌታም ጠየቀው “***እዚህ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ?***” አንድሪውም መለሰ “*እዚህ በጣም ረዥም ጊዜ ሆኖኛል።*” ሰውየውም ታሪክ መተረክ ጀመረ። በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በነበረበት ጊዜ አሥራት የመሰብሰብና ለድሆች የሚሰራጭ ገንዘብን የመቆጣጠር ኀላፊነት እንደነበረው ተናገረ። ቢሆንም ግን ብሩን ይሰርቅ ነበር። ጌታም በርህራሄ በተሞሉ ዓይኖች ሰውዬውን ጠየቀው “***አንዲሪው፥ ወንጌልን ሰምተህ ታውቃለህ?***” አንድሪውም መለሰ “*አዎን ጌታ ሆይ፥ አንድ ክርስቲያን ሴት ነበረች፥ አንድ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥታ ወንጌልን ሰብካ ነበር፤ ነገር ግን ልቀበለው አልፈለግሁም ነበር። ላምነው አልፈለኩም ነበር፥ ነገር ግን አሁን አመንክሁት! አሁን ይሄ እውነት እንደሆነ አምናለሁ! እባክህ ጌታ ሆይ ከእዚህ ቦታ አውጣኝ፥ቢያንስ ለአንድ አፍታ!*”

እያወራ ሳለ ትሎች በዓይኖቹ እየገቡ በጆሮው ይወጣሉ፥ እንደገና ደግሞ ተመልሰው በአፉ ይገባሉ። በእጁ ጎትቶ ሊያወጣቸው ይሞክራል ግን የማይቻል ነው። በአስፈሪ ሁኔታ ይጮህና፥ ከእግዚአብሔር ምህረት ይለምን ነበር። በተደጋጋሚ ጌታ ከዚያ ቦታ እንዲያወጣው መጠየቅ ቀጠለ። ጭራሽ የባሰው፥የሚያሰቃዩትና በጦራቸው የሚወጋጉት ሰይጣኖች ነበሩ። ሰይጣኖቹ ልክ እዚህ ምድር ላይ “**ዘ ጆርዳኖስ**” ተብለው የሚጠሩትን ዓይነት የመጫዎቻ አሻንጉሊቶች ይመስላሉ። እነዚያን አሻንጉሊቶች በሲዖል አይቻቸዋለሁ፥ ነገር ግን አሻንጉሊቶች አልነበሩም፥ ህያው የሆኑ ሰይጣኖች ነበሩ እንጂ። ቁመታቸው ወደ 3 ጫማ የሚጠጋ እና በጣም ስለታም ጥርሶች ነበሯቸው። ከአፋቸው ደም ይወጣ ነበር፥ ዓይኖቻቸው ደግሞ ሙሉ በሙሉ ቀይ ነበሩ።

አንድሪውን በኃይል ይወጉት ነበር፥ እንዲሁም ደግሞ በዚህ የሲያል ክፍል ያሉትን ሁሉ። እነዚህን ሳይ ጌታን በምድር ያለ አሻንጉሊት እንዴት ይህን ሰይጣን ሊመስል እንደቻለ ጠየቅሁት። ጌታም እነዚህ የኃዘን መናፍስት እንደሆኑ ነገረኝ።



ስንቀጥል፥ ሺሆች ሰዎችን ሲሰቃዩ ዓየን። በማንኛውም ጊዜ የሆነች ነፍስ ጌታን ስታይ እርሱን ለመያዝ የሰለለ እጇን ትዘረጋለች። ከዚያም አንዲት ሴት ጌታን እንዳየች ስትጮህ አስተዋልሁ። እንዲህም እያለች ጮኸች *"ጌታ ሆይ፥ እባክህ ማረኝ! ከዚህ ቦታ አውጣኝ!"* በጣም እየተሰቃየች ነበረ እናም እጇን ወደ ጌታ ዘረጋች። ቢያንስ ለአንድ ሰከንድ እንኳን ከዚያ እንዲያወጣት ልመናዋን ቀጠለች። ሙሉ በሙሉ እራቁቷን ሆና በጭቃ ተሸፍና ነበር። ጸጉሯ በጣም ቆሽሾ ነበር እናም ትሎች በሰውነቷ ላይ ከላይ ወደ ታች ይንሸራሸሩ ነበር። በእጆቿ እያነሳች ትጥላቸዋለች፥ ነገር ግን ይህን ባደረገች ቁጥር ጭራሽ እጅግ እየተባዙ ይመጡ ነበር። ትሎቹ ከ6-8 ኢንች ርዝማኔ ነበራቸው። የጌታ ቃል እንዲህ ይላል (ማርቆስ 9፡44) "*ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት*"

ትሎቹ ቦጫጭቀው ሲበሏት ይህችን ሴት ማየትና ልቅሶዋን መስማት እጅግ ይዘገንናል። ከደረቷ ጋር የተጣበቀ በእሳት የማይጠፋ የብረት ሰሀን አለ። እንዲህም ይላል "**እዚህ ያለሁት ስለዝሙት ነው።**" እንደ ኃጢአቷ ዓይነት፥ ይህች ሴት በሲያል እጅግ ከሚያስጸይፍ ወፍራም እባብ ጋር ዝሙት እንድትፈጽም ትገደዳለች። እባቡ ከ6-8 ኢንች የሚደርሱ ትላልቅ እሾኾች በሰውነቱ ዙሪያ ነበሩ። እባቡ በሀፍረተ ሥጋዋ ገብቶ በሰውነቷ ውስጥ እስከ ጉሮሮዋ ድረስ ወደ ላይ ይወጣል። ልክ ሰይጣኑ ሲገናኛት መጮህ ጀመረች።

ጌታን ከዚያ ቦታ እንዲያወጣት አምርራ ጠየቀችው *"ጌታ ሆይ፥ እዚህ ያለሁት በዝሙት ምክንያት ነው፥ በኤድስ ከሞትኩ ጀምሮ እዚህ ለ7 ዓመታት ቆይቻለሁ። ስድስት ፍቅረኞች ነበሩኝ፥ እናም በዝሙት ምክንያት እዚህ አለሁ።"* በሲያል የግድ ኃጢአቷን ትደጋግመዋለች። ቀን ወይንም ማታ ምንም እረፍት አልነበራትም፤ ሁል ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ትሰቃያለች። እጆቿን ወደ ጌታ ለመዘርጋት ሞከረች፥ ነገር ግን ጌታ እንዲህ አላት "***ብላንካ፥ ለአንቺ ረፍዶብሻል። መኝታሽ ትሎች ይሆናሉ፥ ትሎችም የሸፍኑሻል።***" (ኢሳይያስ 14፡11) ጌታ ይህንን በተናገረ ጊዜ እሳት እንደ ብርድልብስ ሸፈናት ከዛ በኋላ አላየኋትም።

ሺሆችና ሺሆች ሲሰቃዩ እያየን ጉዟችንን ቀጠልን። ወጣቶች፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች ሁሉ ይሰቃዩ ነበሩ። ከዚያም ትልቅ የእሳት መዋኛ ገንዳ የሚመስል ቦታ ደረስን፥ ሺሆች ሴቶችና ወንዶች በውስጡ ነበሩ። በሁሉም ደረት ላይ እንዲህ የሚል የብረት ሰሀን አለ "**እዚህ ያለሁት አስራትና ምጽዋት ባለመስጠቴ ነው።**" ይህንን እንዳነበብሁ ጌታን ጠየቅሁት *"ጌታ ሆይ፥ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እንዴት በዚህ ምክንያት ሰዎች እዚህ ይመጣሉ??"* ጌታም መለሰልኝ "***አዎ፥ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች በሕጌ ተጽፎ ሳለ እንደማያስፈልግ ስለቆጠሩ ነው።***" (ሚልክያስ 3፡8-9) እንዲህ ይላል "*ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም፥ የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በበኵራት ነው። እናንተ፥ ይህ ሕዝብ ሁሉ፥ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ።*"

ጌታም ሰዎች ምጽዋትን ሲያቆሙ፥ የጌታን ሥራ ያደናቅፋል፥ እናም ወንጌል አይሰበክም። በዚህ ቦታ ያሉ ሰዎች ከሌሎቹ በሺህ እጥፍ የከፉ ይሰቃያሉ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቃል እያወቁ ስላላከበሩት ነው።

ጉዟችንን ቀጠልን እናም ጌታ የሆነ ሰው አሳየኝ። ከወገቡ እስከ ራሱ ይታየኛል፥ ከዛም እንዴት እንደሞተ ማየት ጀመርሁ። ስሙ ሮጌሊኦ ይባል ነበር። የሆነ ሰው ወንጌልን ሊሰብከው ወደ እርሱ ቀርቦ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሰጠው በመኪናው ውስጥ ነበር። ሮጌሊኦ ግን የዚያን ሰው ማስጠንቀቂያ ቸል ብሎ ጉዞውን ቀጠለ፥ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መኪናው እንደሚገለበጥ አላወቀም። ወደ ገደል ውስጥ ተከሰከሰ እናም ወዲያው ሞተ።

በሞተበት አፍታ መጽሐፍ ቅዱሱ [ራዕይ 21:8] ላይ ተገለጠ “*ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።*” ልክ ሮጌሊኦ ይህን ጥቅስ እንዳነበበ ሞተና ወደ ሲኦል ወረደ።

እዚያ ከገባ ገና አንድ ወሩ ነበር እናም እስካሁን ፊቱ ላይ ትንሽ ሥጋ ነበረው። ቢሆንም ግን እንደማንኛውም ሰው እየተሰቃየ ነበር። በመጀመሪያ ለምን ሲያል እንደነበረ እራሱ አላወቀም። በእኔ ግምት፥ ያ ክርስቲያን ወደ እርሱ ሲቀርብ፥ ጌታ ኢየሱስን ለመቀበል ብቸኛውና የመጨረሻ እድሉ ነበር። በተመሳሳይ መልኩ አብዛኞቹ እርሱን ለመቀበል እድል ነበራቸው። ዛሬ፥ ልባችሁን ለእርሱ እንድትከፍቱ እጋብዛችኋለሁ፤ እርሱ ብቻውን መንገድ፣ እውነትና ህይወት ነው። [(ዮሐንስ 14:6)] ወደ መንግሥተ ሰማያት ልንድን የምንችለው በእርሱ ብቻ ነው። [(ሐዋርያት 4:12)] ጌታ ራሱ የእርሱን መንገድ በቅድስናና በታላቅ ክብር እንድንከተል ይጠይቀና፡፡
እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

---

# --- (4[ኛ] ምስክርነት) ---

*ወንድሞች እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ጌታ እጄን በያዘው ጊዜ አለት ላይ እንደነበርኩ ይታወቀኛል፥ እናም ከኋላችን መልአክ አየሁ። በሚገርም ፍጥነት በዋሻው ውስጥ በሚገርም ፍጥነት ቁልቁል መሔድ ጀመርን። በፍጥነት ወደ ኋላ ተመለከትሁና መልአኩ እንደሔደ አየሁ፥ እናም በጣም ፈርቼ ነበር። ጌታንም ጠየቅሁት “ጌታ ሆይ፥ መልአኩ የታለ? ለምንድን ነው በዚህ ከእኛ ጋር የሌለው?” ጌታም እንዲህ አለኝ “**እኛ ልንሄድበት ወዳለው ቦታ ሊሄድ አይችልም**”*

*ወደታች መሄድ ቀጠልንና ልክ እንደ ሊፍት ድንገት ቆምን። ብዙ ዋሻዎችን አይቻለሁ፤ እናም እህቴ ሳንድራ በተናገረችው በአንዱ ዋሻ ውስጥ አለፍን፣ ያ ሰዎች በጭንቅላታቸው በመንጠቆ በእጃቸውም በእግር-ብረት ተንጠልጥለውበት የነበረው ዋሻ። ሰዎች የነበሩበት ግድግዳ ርዝመቱ የማያልቅ ይመስላል። ሚሊዮኖች ሰዎች ተንጠልጥለውበት ነበር። በመላ ሰዉነታቸው ላይ ትሎች ነበሩባቸው። ወደ ፊት ሄድ አልኩና ያንኑ የሚመስል ሌላ ግድግዳ እንደነበረ አየሁ። ለጌታ እንዲህ አልኩት “ጌታ ሆይ፥ በዚህ ቦታ ብዙ ሰዎች አሉ!” በድንገት የማላስታውሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በአይምሮዬ መጣ። ጌታ እንዲህ አለኝ “**ገሃነምና ሲዖል ሁል ጊዜ እንደተራቡ ናቸው።**” [(ምሳሌ 27:20)]*



*ያን ቦታ ትተን “**የጋኖች ሸለቆ**” ብለን የሰየምነው ቦታ ደረስን። እነዚህ ጋኖች በሚንተከተክ ጭቃ የተሞሉ ናቸው፥ እናም ወደ አንዱ ቀረብን፡፡ መጀመሪያ ያየሁት ሰው ሴት ናት። በሚፈላው ጭቃ ውስጥ እየተንሳፈፈች ትሰምጣለች፥ ነገር ግን ጌታ ባያት ጊዜ መንቀሳቀሷን አቁማ በወገቧ ልክ መንሳፈፍ ጀመረች። ጌታም ጠየቃት “**አንቺ ሴት፥ ስምሽ ማነው?**” እርሷም “ስሜ ሩቤላ (Rubiella) ነው።” ብላ መለሰች። ጸጉሯ በሚፈላው ጭቃ ተሞልቷል፥ እናም በእሳቱ ክስል ብለው የጠቆሩ ሥጋዎች በአጥንቷ ላይ ተንጠልጥለዋል። ትሎች በዓይኗ ቀዳዳ ገብተው በአፏ ይወጣሉ፥ እንደገና በአፍንጫዋ ይገቡና ደግሞ በጆሮዋ ይወጣሉ። ትሎቹ መግባት ሲያቅታቸው በሰውነቷ ላይ ቀዳዳ ይሠራሉ፥ በዚህ ጊዜ ሊገለጽ የማይቻል ህማም ይሰማታል።*

“*ጌታ ሆይ ÷ እባክህ! ከዚህ ቦታ አውጣኝ። ይቅር በለኝ! ከዚህ በኋላ እንደዚህ መቀጠል አልችልም! አቁመው ጌታ ሆይ! ልቋቋመው አልቻልኩም! እባክህ ማረኝ!*” ብላ ጮኸች። ጌታም ለምን ወደዚህ ስፍራ እንደገባች ጠየቃት። እርሷም በኩራት ምክንያት እንደሆነ ተናገረች÷ በደረቷ ላይም ያለው የብረት ሳህን እንደዛ ይል ነበር። በእጇ መደበኛ የሚመስል ጠርሙስ ነበር÷ ለእርሷ ግን ውድ ሽቶ ነበር የሚመስላት። ሩቤላ በአሲድ የተሞላውን ጠርሙስ እያነሳች በሰውነቷ ላይ ትነፋዋለች። ይህም ሥጋዋ እየተበጣጠሰ እንዲወድቅ ያደርገዋል÷በዚህም ከፍተኛ ህመም ይሰማታል።

እንዲህ ብላም ወደ ጌታ ጮኸች “*ጌታ ሆይ እባክህ÷ ማረኝ! ከዚህ በኋላ እዚህ መቆየት አልችልም! ለአንድ ሰከንድ ብቻ ጌታ ሆይ።*” ሽቶ መጠቀም ኃጢአት ነው እያልኩ አይደለም÷ ነገር ግን ጌታ ሴትየዋ በሽቶዋ ምክንያት በዚህ እንዳለች ነግሮናል። የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ይላል [(ዘጸ.5:7)](ዘጸ.5:7) “***ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።***” በዚህ ያለችው በህይወቷ ውስጥ ቅድሚያ የነበራቸው÷ ውበቷ፣ ሽቶዋና ኩራቷ ስለነበሩ ነው። ምንም ቢሆን ጌታ ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ ነው! በህይወታችሁ ውስጥ አንደኛ (ቀዳሚ) መሆን አለበት፤ ለዚህ ነው እርሷ በዚህ ያለችው። በኃዘን ተመለከታትና እንዲህ አላት “***ሩቤላ አሁን ላንቺ ረፍደል÷ ትሎች መኝታሽ ይሆናሉ÷ ትሎችም ይሸፍኑሻል።***” ጌታ ይህን ባላት ጊዜ እሳት እንደ ብርድልብስ ሸፈናት። ሰውነቷ በጋኑ ውስጥ እየሰመጠ ባለበት ሰዓት እጅግ ዘግናኝ ህማም ተሰማት።

ከዚያ ቦታ ርቀን ሄድንና ግዙፍ በሮች ያሉበት ቦታ ደረስን። ስንቀርባቸው ተከፈቱልን። በአንዱ በኩል ትልቅ ዋሻ አየን። ሳይ÷የተለያየ ቀለም ያላቸው ብርሃኖች እንደ ጢስ ጉም መስለው ሲሄዱ አየሁ። በድንገት ሙዚቃ ሰማን÷ ሳልሳ፣ ባሌናቶ፣ ሮክ እና ሰዎች በሬድዮ የሚሰሟቸው የተለያዩ ታዋቂ ሙዚቃዎች። ጌታም እጁን አንቀሳቀሰ÷ እናም ሚሊየኖችና ሚሊየኖች ሰዎች በእጃቸው በሰንሰለት ተሰቅለው በእሳቱ ውስጥ እንደ እብድ ሲዘሉ አየን።

ጌታም እኛን እያየ እንዲህ አለ “***ተመልከቱ ይህ የዳንሰኞች/ጨፋሪዎች ዋጋ ነው።***” በሙዚቃው ምት ልክ እንደ እብድ ወደላይና ወደታች ይዘላሉ። ሳልሳ ከሆነ ሙዚቃው÷በዛ ምት ልክ ይዘላሉ÷ ሌላም ሙዚቃ ከሆነ በዛ ሙዚቃ ምት ልክ ይዘላሉ። መቼም መዝለላቸውን አያቆሙም። ግን ከዛ የሚከፋው ጫማቸው ከስሩ ባለ 6 ኢንች ሚስማር አለ። በዘለሉ ቁጥር እግራቸውን ይወጋቸዋል÷እናም መቼም እረፍት የላቸውም። የሆነ ሰው ሊቆም ሲሞክር÷ አጋንንቶቹ በፍጥነት መጥተው በጦር እየወጉ እንዲህ እያሉ ይረግሟቸዋል “*አመስግኑት! አሁን የእናንተ መንግሥት ይሄ ነው÷ ሰይጣንን አመስግኑት! አመስግኑት! ማቆም አትችሉም÷ አመስግኑት! አመስግኑት! ማመስገን አለባችሁ! መዝለል አለባችሁ! መጨፈር አለባችሁ! ለአንድ ሰከንድ እንኳን ማቆም አትችሉም።*”

በጣም የሚያሳዝነው አብዛኞቹ ሰዎች ጌታን የሚያውቁት ክርስቲያኖች መሆናቸው ነው÷ነገር ግን በሞቱ ጊዜ በምሽት ክበቦች ነበሩ። ምን አልባት እንዲህ ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል “*የቱ ጋር ነው በመጽሐፍ ቅዱስ መጨፈር ኃጢአት ነው የሚለው?*” በ[ያዕቆብ 4፡4](ያዕቆብ 4፡4) ላይ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል “***አመንዝሮች ሆይ÷ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።***” እንዲሁም [1ዮሐ.2:15-17](1ዮሐ.2:15-17) “***ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ÷ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።***” አስታውሱ ዓለም ያልፋል÷ ይህ ሁሉ ይጠፋል÷ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን እስከ መጨረሻው ይጸናል።

ጓደኞቼና ወንድሞቼ÷ ይህን ቦታ ለቀን እንደወጣን÷ሲያልን ወደ ተለያየ የስቃይ ዓይነቶች የሚከፋፍሉ ድልድዮችን አየን። በእግረኛ ድልድይ ላይ የሚሄድ መንፈስ አየን። ልክ ምድር ላይ ያየነውን አሻንጉሊት ይመስላል÷የሀብት ጭራቆች እንላቸዋለን። የተለያየ ቀለም ያለው ጸጉር፣ እንደ ሽማግሌ ዓይነት ፊት ግን የህፃን ልጅ ዓይነት ሰውነት አላቸው፤ ነገር ግን ጾታዊ አካል የላቸውም። ዓይኖቻቸው በክፋት የተሞላ ነው። ጌታም እነዚህ የማጣት መናፍስት እንደሆኑ አስረዳን። ይህ መንፈስ በእጁ ጦር ይዞ በዛ በእግረኞች ድልድይ ላይ በልበ ሙሉነት ይራመድ ነበር÷ አካሄዱ ልክ እንደ ንግሥት አልያም እንደ ቆንጆ ሞዴል።

ሲሄድ ከጦሩ ስር ያሉትን ሰዎች ይወጋቸዋል። እንዲህም እያለ ይረግማቸዋል “*በክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ቆማችሁ መግባት ያልፈለጋቹባትን ቀን አስታወሳችሁ? እነርሱ ሲሰብኩላችሁ እናንተ ግን ለመስማት ያልፈለጋችሁባትን ቀን አስታወሳችሁ? የወንጌል በራሪ ጽሑፎችን በሰጧችሁ ጊዜ የወረወራችሁበትን ቀን አስታወሳችሁ?*” የጠፉትም ነፍሳት ጆሯቸው የነበረበትን ቦታ ለመሸፈን ይሞክራሉ። ለጋኔሉ ይመልሱለታል “ *ዝም በል! ዝም በል! ከአሁን በኋላ አትንገረኝ! ከዚህ የበለጠ ማወቅ አልፈልግም፥ ዝም በል!* ” ነገር ግን ክፉ መንፈስ በነፍሶቹ ላይ የሚፈጥረውን ህመም እያየ ይደሰት ነበር።



ከጌታ ጋር መሄዳችንን ቀጠልን። ብዙ ሰዎችን እያየን ሳለ፣ እሳቱ ውስጥ ካሉት ሰዎች ሁሉ አብልጦ የሚይጮህ አንድ ሰው አስተዋልን። እንዲህ ይል ነበር “*አባት ሆይ፣ አባት ሆይ ማረኝ!* ” ጌታ ሰውየውን ማየት አላቆመም ነበር፣ ነገር ግን “አባት ሆይ” የሚለውን ቃል በሰማ ጊዜ ተሸበረና ፊቱን አዞረ። ኢየሱስ ወደእሱ ተመለከተና ይህን ነገረው “***አባት ሆይ? አባት ሆይ ብለህ ትጠራኛለህ? እኔ የአንተ አባት አይደለሁም፥ አንተም የእኔ ልጅ አይደለህም። ልጄ ብትሆን ኖሮ በመንግሥተ ሰማያት ከእኔ ጋር በሆንክ ነበር። አንተ የአባትህ የሰይጣን ልጅ ነህ።***” ወዲያውም እሳት እንደ ብርድልብስ መጥቶ ሸፈነው።

ጌታም የዚህን ሰው ህይወት ነገረን። ሰውየው አባት ሆይ ብሎ የጠራው ያውቀው ስለነበር ነው። ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄድና እግዚአብሔርን በቃሉ ውስጥ ይሰማው ነበር፥ እናም ብዙ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች ተቀብሏል። ስለዚህ ጠየቅን “*ምን ተፈጠረ ጌታ ሆይ? ታዲያ እንዴት ወደዚህ ሊገባ ቻለ?*” ጌታም መለሰ “***ሁለት ዓይነት ህይወት ይኖር ነበር፥ በቤተ ክርስቲያን ሌላ ህይወት በቤቱ ሌላ ህይወት። በልቡ እንዲህ ብሎ ያስብ ነበር ‘ባጠገቤ ማንም የሚኖር የለም፥ ፓስተሬም ወይም ሌላ ወንድም፥ ስለዚህ የፈለኩትን ማድረግ እችላለሁ።’ ነገር ግን የጌታ ዓይኖች በሁሉም ቦታ እንዳሉና መንገዳችንን ሁሉ እንደሚያዩ እና ማንም ከጌታ ሊደበቅ ወይም ሊዋሸው እንደማይችል እረስቶ ነበር።***”

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን “***አትሳቱ፣ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና***” (ገላትያ 6:7) ይህ ሰው ከሌሎቹ ሺህ እጥፍ የከፋ ይሰቃይ ነበር። እጥፍ ፍርድን እየከፈለ ነበር፤ አንዱ ስለኃጢአቶቹ፣ ሌላው ደግሞ ጌታን ለማታለል እንደሚችል ስለማሰቡ።

ዛሬ ሰዎች ኃጢአትን ለማበላለጥ ይሞክራሉ፤ ግብረሰዶማውያን፣ ሌቦችና ነፍሰ ገዳዮች ከውሸተኞችና ከሀሜተኞች የበለጠ ኃጢአተኞች እንደሆኑ አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን፥ በጌታ ዓይን ሁሉም ኃጢአቶች እኩል ዋጋና እኩል ፍርድ አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን “*የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና*” “*ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች*” (ሮሜ.6:23) (ሕዝቅኤል18:20) ጓደኞቼና ወንድሞቼ፥ የጌታን ግብዣ ትቀበሉ ዘንድ እጋብዛችኋለሁ። ከተጸጸታችሁ ጌታ የምህረት አጆቹን ዘርግቶላችኋል። የጌታ ቃል እንደሚነግረን አካሄዱን የቀየረና የተመለሰ ምህረት ይሰጠዋል። በኋላ በግድ እስከምናውቀው ድረስ ከመጠበቅ አሁን ማመን እጅግ በጣም የተሻለ ነው። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

---

# --- (5ኛ ምስክርነት) ---

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ሮሜ.6:23 "*የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።*"

ወደዛ ስሄድ ህመምና ሞት ምን እንደ ሆነ ገባኝ። ባየሁት ነገር በጣም ፈርቼ ነበር። እዛ ብዙ ብዙ ሰዎች እንዳሉ ተረዳሁ፤ ሁሉም ያለቅሱና ይጮኹ ነበር። ሙሉ በሙሉ ጨለማ ነበር፥ ነገር ግን የጌታ በዚያ መኖር ጨለማውን አጠፋው። ሺሆችና ሺሆች ነፍሳት በዚያ እርዳታንና ምህረትን በለቅሶ ሲለምኑ አየን። ከዚያ እንዲያወጣቸው ወደ ጌታ በለቅሶ ይጮኹ ነበር። እኛ እራሳችን ከባድ ህማም ተሰማን ምክንያቱም ጌታ ባያቸው ቁጥር በኃይል ይጎዳ እንደነበር ስላወቅን ነው።

ብዙዎች ጌታ ለደቂቃ እንኳን፥ ለሰከንድ እንኳን እንዲያወጣቸው በለቅሶ ይለምኑት ነበር። ጌታም ይጠይቃቸዋል "*ለምን መውጣት ፈለጋችሁ?*" እነርሱም ይመልሱለታል "*ምክንያቱም መዳን ስለምፈልግ ነው! ንሰሐ መግባትና መዳን ስለምፈልግ ነው!*" ሆኖም ግን ለእነርሱ አሁን ረፍዷል።

እየሰማችሁኝ ያላችሁ ውድ ሰዎች፥ ዘላለማዊ እጣችንን ለመወሰን ያለን እድል አሁን ነው። ለዘላለም የመዳንን ህይወት መምረጥ ትችላላችሁ አልያም የዘላለምን የፍርድ ህይወት።

በደንብ ወደታች ወረድን። እየሄድንበት የነበረው መሬት በእሳቱ ሲጠፋ አየሁ፤ ጭቃና እቶን ከውስጡ ይወጡ ነበር። እንዲሁም መጥፎ ሽታ በየቦታው ነበር። ከሰዎቹ ጩኸትና ከሽታው የተነሳ የመበሳጨትና የማቅለሽለሽ ስሜት ተሰማን።



በሚነደው ጭቃ ውስጥ ከወገብ በታች የጠለቀ ሰው ከሩቅ አየን። እጁን ባወጣ ቁጥር ሥጋ ከአጥንቱ ላይ ወደ ጭቃው ይወድቅ ነበር። በአጽሙ ውስጥ ግራጫማ ጭስ አየንና ጌታን ምን እንደሆነ ጠየቅነው። እንደዚህ ዓይነቱ ጭስ በሲዖል ባሉ በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ነበረ። እርሱም ነፍሳቸው ትንሽ በሆነ ሰውነት ውስጥ ታግታ እንደ ሆነ ነገረን፥ ልክ እንደተጻፈው ራዕ.14:11 "*የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፥ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም።*"

በምድር ላይ ቸል ስንላቸው የነበሩትን ብዙ ነገሮችን መረዳት ጀመርን፤ በጣም ጠቃሚው ግልጽ የሆነልን ነገር፥ በምድር ላይ ያለው ህይወታችን ዘላለማዊ ህይወታችንን በየት እንደምናሳልፍ ይወስናል።

ከጌታ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን ስንሄድ፥ በሲዖል ውስጥ የተለያዩ የስቃይ ደረጃዎች ያሉባቸው ቦታዎች እንዳሉ ተረዳን። የተሰቃዩ ነፍሳት ወዳሉበት ትናንሽ ክፍሎች መጣን። ነፍሶቹ በተለያዩ ጋኔሎች ይሰቃዩ ነበር። ጋኔሎቹ ሰዎቹን እንዲህ እያሉ ይረግሟቸው ነበር "*እናንተ የተረገማችሁ እርኩሳን፥ ሰይጣንን አመስግኑት! በምድር ላይ ስታገለግሉት እንደነበር እዚህም አገልግሉት!*" ነፍሶቹ ከትሎቹ የተነሳ በአሳዛኝ ሁኔታ ተጎድተው ነበር፤ እሳቱም በመላ ሰውነታቸው ላይ እንደ አሲድ ነበር።

በአንድ የእስር ቤት ክፍል ውስጥ ሁለት ወንዶችን አየን፥ በእጃቸውም ጩቤ ይዘው እርስ በእርሳቸው ይወጋጉ ነበር። እርስ በእርሳቸውም እንዲህ ይባባላሉ "*አንተ የተረገምህ እርኩስ! ባንተ ምክንያት ነው እዚህ የገባሁት! አንተ ነህ ወደ እዚህ እንድመጣ ያደረግኸኝ ምክንያቱም እውነቱን እንዳላይ ዓይኔን አሳውረህ ጌታን*

*እንዳላውቀው አድርገሽኛል! እርሱን እንድቀበለው አላደረግሽኝም! ብዙ ጊዜ እድሉ ነበረኝ አንተ ግን እንድቀበለው አላደረግሽኝም! ሌትና ቀን እየተሰቃየሁ በዚህ ያለሁት በዚያ ምክንያት ነው!"*

ጌታ በራዕይ በምድር የነበረውን ህይወታቸውን አሳየን። መጠጥ ቤት ውስጥ አንድ ላይ አየናቸው። ወደ ጠብ ያመራ ክርክር ተጀመረ። መጀሪያውኑም ሰክረው ነበር። አንደኛው የተሰበረ ጠርሙስ ወሰደ ሌላኛው ደግሞ ቢላ አወጣ። እያንዳንዳቸው እስከሞት ድረስ እስኪቆስሉ ድረስ ተወጋጉና ሞቱ። ሁለቱ ሰዎች እስከዘላለም ይህን ክስተት እንዲደጋግሙት ተፈርዶባቸዋል። እንዲሁም ደግሞ እርስ በእርሳቸው ባላቸው ፍቅር እንደ ወንድማማች የነበሩ የቅርብ ጓደኛሞች እንደነበሩ እያስታወሱ ይሰቃዩ ነበር።

*ዛሬ ልነግራችሁ የምፈልገው፥ አንድ እውነተኛ ጓደኛ አለ ስሙም የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ ጓደኛ ነው። በማንኛውም ጊዜ ከእናንተ ጋር ያለ ታማኝ ጓደኛ እርሱ  ነው።*

ጉዟችንን ስንቀጥል በአንድ እስር ቤት ክፍል ውስጥ አንዲት ሴት አየን፥ሴቲቱም በጭቃ ላይ እየተንከባለለች ነበር። ጸጉሯ እንዳለ ተመሰቃቅሎ በጭቃ ተለውሷል። በዛው ክፍል ውስጥ ትልቅ ወፍራም እባብ ነበር። ወደ እርሷ ቀረበ፣ ተጠመጠመባት፣ ከዛም ከታችኛው የሰውነቷ ክፍል ጀምሮ ወደ ውስጧ መግባት ጀመረ። ከዛ እባብ ጋር ፆታዊ ግንኙነት እንድታደርግ ትገደድ ነበር። በሴሰኝነት የኖሩ ወንዶችም ሴቶችም በዚያ ቦታ እንዲደጋግሙት ይገደዱ ነበር። ሆኖም ግን ይህን የሚያደርጉት 6 ኢንች እሾኽ በሰውነታቸው ላይ ካለባቸው እባቦች ጋር ነው። እባቡ ሰውነቷ ውስጥ በገባበት በእያንዳንዱ ጊዜ ሰውነቷን ያወድመው ነበር። ወደ ጌታ በለቅሶ እየጮኸች እንዲያቆመው ትጠይቀው ነበር። ከዚህ በላይ መሰቃየት አትፈልግም። "*አስቁመው! ድጋሚ አላደርገውም አስቁመው! እባክህ! አስቁመው!"* እባቡ በተደጋጋሚ በውስጧ እየገባ ሰውነቷን ሲያወድመው ጌታን ለመነችው።

ለቅሶዋን ላለመስማት ጆሯችንን ሸፈንን ነገር ግን ይሰማን ነበር። የባሰ ጆሯችንን ለመድፈን ሞከርን ግን ምንም አልረዳንም። ለጌታም እንዲህ አልነው "*እባክህ ጌታ ሆይ፥ ከእንግዲህ ወዲያ ይህን ማየትም ሆነ መስማት አንፈልግም! እባክህ!"* ጌታም አለ "***ለሌሎች እንድትነግሩ ይህን ማየት ያስፈልጋችኋል፥ምክንያቱም ሕዝቤ እየጠፉ ነው፥እውነተኛውን መዳን ሕዝቤ ችላ እያለ ነው፥እውነተኛውን የመዳን መንገድ።"***

መሄዳችንን ቀጠልንና ሺሆችና ሺሆች ሰዎች በእቶኑ ውስጥ ያሉበት ግዙፍ ሐይቅ አየን። ለእርዳታ እጃቸውን አወዛወዙ፥ ነገር ግን በቦታው ላይ ብዙ አጋንንት ይበሩ ነበር። እነዚህ ጋኔሎች በዚያ ሐይቅ ውስጥ S-ቅርጽ በነበረው ጦር ያሰቃዩአቸው ነበር። ጋኔሎቹ እንደዚህ እያሉ ያሾፉባቸውና ይረግሟቸው ነበር "*የተረገማችሁ እርኩሶች! አሁን ሰይጣንን ማምለክ አለባችሁ! አመስግኑት፥ ምድር ላይ ስታደርጉ እንደነበራችሁት አመስግኑት*" በዚያ ሺሆችና ሺሆች ሰዎች ነበሩ። በጣም ፈርተን ነበር፥ የጌታን እጅ ይዘን ባይሆን በዚያ አስፈሪ ቦታ እንደምንቀር ተሰማን። ይሰማን ከነበረው ስሜት የተነሳ በጣም ተሸበርን።

በሩቁ በከባድ ህመምና ስቃይ ውስጥ የነበረ ሰው ቆሞ አየን። ሁለት አጋንንት በላዩ እየበረሩ ያሰቃዩት ነበር። በጦራቸውን ሰውነቱን እየቆፈሩ ጎድኖቹን ያወጡ ነበር። በሁሉም ጊዜ ያሾፉበት ነበር። ይባስ ብሎ በምድር ላይ ስለቀሩት ቤተሰቦቹ ሁልጊዜ እያሰበ እንደሚሰቃይ ጌታ አሳየኝ። ሰውየው ቤተሰቦቹ ወደ ተመሳሳይ የስቃይ ቦታ እንዳይገቡ ይፈራ ነበር። ይፈራ የነበረው የመዳንን መልዕክት ነግሯቸው ስላማያውቅ ነው። የሚሰቃየው ይህን መልዕክት የሚቀበሉበት እድል እንደ ነበረ አስታውሶ ነው። ይህን መልዕክት ለቤተሰቦቹ ለመናገር በጣም አስፈላጊ ሰው ነበር፥ ነገር ግን ቸል ማለትን መረጠ፥ እናም አሁን ስለ ወንዶች ልጆቹና ስለሚስቱ ይጨነቃል።

ስቃዩ ቀጥሎ አጋንንቶቹ እጁን ቆረጡት፥ ወደሚነደው ጭቃ ውስጥም ወደቀ። ከሚቃጠለው ጭቃ የተነሳ ባለበት ህመም እንደ ትል ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ተመላለሰ። ከግለቱ የተነሳ ሥጋው ከአጥንቱ ላይ ወደቀ። ከዚያም ከዛ ቦታ ለመውጣት እንደ እባብ መሳብ ጀመረ። ነገር ግን በየጊዜው አጋንንቱ ወደ ውስጥ ይገፈትሩትና የባሰ በጭቃ ውስጥ ጠልቆ ይገባል።

ከዚያ ብዙ ጋኔሎች በአንድ ቦታ አየን። የሆነ ነገር ትኩረቴን ሳበው፥ አንዱ ጋኔል አንድ ክንፍ የለውም ነበር። ጌታን ጠየኩት "*ጌታ ሆይ፥ ለምንድን ነው አንድ ክንፍ የሌለው?*" ጌታም አለኝ "***ጋኔሉ ለአንድ አላማ ወደ ምድር ተልኮ ነበር፥ ነገር ግን ሥራውን አልተወጣም፥ እናም በአንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ሲያል ተመልሶ ተጣለ። በዚህም ሰይጣን መጥቶ ቀጣው፥ አንዱን ክንፉንም ቆረጠው።***" ከዚያም እንደ ክርስቲያን፥ በኢየሱስ ስም ጋኔኖችንና አጋንንትን ልናስወጣ ሁሉ ኃይልና ስልጣን እንዳለን ተረዳን።

እነዚህን ቃላት በአሁኗ ሠዓት የምትሰሙ ውድ ጓደኞቼ፥ ይህ ምስክርነት ለፍርድ ሳይሆን ለድኅነት ነው፤ ስለዚህም ራሳችሁን ልትፈትሹና በጌታ ፊት ልባችሁ ያለበትን ሁኔታ እንድታውቁ ነው። ይህ፥ አካሄዳችሁን ለፍርድ ሳይሆን ለድኅነት እንድትቀይሩ ነው። አሁኑኑ ልባችሁን ወደ ጌታ አንስታችሁ ኃጥያታችሁን ተናዘዙ፥ ጌታ በዚህች አፍታ ቢመጣ ከእርሱ ጋር እንድትሄዱ፥ ነገር ግን ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት የስቃይ ቦታ እንዳትሄዱ። ያኔ ጌታ ለምን በእጸ መስቀል ላይ ታላቅ ዋጋ እንደ ከፈለ ትረዳላችሁ።

በሲያል ለምን እንደ ገቡ ደንታ ያልነበራቸው ብዙ ሰዎችን ዓየን። ህይወታቸው ኃጢአት ነው ብለው ባላሰቧቸው ተግባሮች የተሞሉ ነበሩ። ውድ ጓደኞቼ፥ እራሳችሁን ፈትሹ! መዋሸት፣ መስረቅ፣ ትምክህተኝነት ምንም አየደለም ብላችሁ እንዳታስቡ! በጌታ እይታ እነዚህ ሁሉ ኃጢአቶች ናቸው! ውድ ወንድሞች፥ ተመለሱና እነዚህን ነገሮች ማድረግ አቁሙ! ይህን መልዕክት የምነግራችሁ በፍቃደኝነት ኃጢአት መሥራትን እንድታቆሙ እንደዉም የጌታን ፊት ይበልጥ እንድትሸት ነው።

---

# --- (6ኛ ምስክርነት) ---

መዝሙር 62:12 "***አቤቱ፥ ምሕረትም ያንተ ነው፤ አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጣለህና።***"

ጢት ላይ ጌታ በዛው ክፍል ውስጥ ጎበኘን፥ እጃችንን ይዞን ወደታች መሄድ ጀመርን። ልቤ በፍርሃት ተሞልቷል፥ ልገልጸው እንኳን አልችልም። እጄን ከአዳኜ እጄ ማላላት እንደሌለብኝ አወቅሁ። ኢየሱስ ሕይወቴና ብርሃኔ እንደሆነ ተሰማኝ እናም ተስፋዬ ሁሉ በእርሱ እንደሆነ፤ አለበለዚያ በዚያ ቦታ ተትቼ እቀራለሁ። መቼም ቢሆን ወደዚያ ቦታ ተመልሼ እሄዳለሁ ብዬ አላሰብኩም። እንደዚህ ዓይነት ቦታም ይኖራል ብዬ አላምንም ነበር። እንደ ክርስቲያን እራሱ፥ ፑርጋቶሪ ሲያል ነው ብዬ ነበር የማምነው፥ ነገር ግን እግዚአብሔር የሲያልን እውነታ አሳየኝ።

ሲያል በደረስን ጊዜ፥ ቦታው ሲናወጽ ተሰማኝ። እናም ሁሉም በዛ ያሉ ጋኔሎች ለመደበቅ ሮጡ፥ ምክንያቱም አንዳቸውም የጌታን በዚያ መሆን ሊቋቋሙት አልቻሉም። የናዝሬቱ ኢየሱስ በዚያ መኖሩን ስላወቁ በእስር ያሉት ነፍሳት እራሳቸው ድምጻቸውን የበለጠ ከፍ አድርገው ሲጮኹ ሰማናቸው። ሁሉም ከዚያ ቦታ ምን አልባት ሊያወጣቸው የሚችለው አንድ ሰው ብቻ እንደሆነ አውቀዋል። ያ ተስፋ ነበራቸው፥ ምንም እንኳን የውሸት ተስፋ ቢሆንም።

ከኢየሱስ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን የሴሰኞች ክልል ደረስን። ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ በእሳት የተሸፈነችን ሴት ለማየት ዞረ። ኢየሱስ ሲያያት ከእሳቱ ቀስ እያለች መውጣት ጀመረች፥ ምንም እንኳን ስቃዩ ባይቀርላትም። እራቁቷን እንደሆነችና ሙሉ በሙሉ የሰውነቷን ክፍል እናይ ነበር። ሰውነቷ ሙሉ በሙሉ ቆሻሻ ነበር፥ እናም የሚገማ ሽታ ነበራት። ጸጉሯ ሁሉ ተመሰቃቅሏል፥ እናም ቢጫማ አረንጓዴ ጭቃ በሰውነቷ ላይ ነበር። ምንም ዓይን የላትም እናም ከንፈሯ ደግሞ ተበጣጥሷል። ከስሎ በጠቆረው አጥንት እጇ የወዳደቀ ሥጋዋን እያነሳች ፊቷ ላይ ለመመለስ ትሞክራለች። ነገር ግን ይህም የባሰ ስቃይ ይሆንባታል።

ከዚያም ተንቀጥቅጣ የባሰ ጮኸች፥ ጨኸቷ መቼም አላቋረጠም። በትሎች ተሞልታ ነበር፥ እናም ደግሞ በእጇ ላይ የተጠመጠመባት እባብ ነበር። የከረረና በሰውነቱ ዙሪያ እሾኽ ነበረበት። በሰውነቷ ላይ 666 የሚለው ቁጥር ታትሞባታል፤ ይህም በራዕይ ላይ የተጻፈው [የአውሬው ቁጥር] ነው። [(ራዕይ 13፡16-18)] እንዲሁም ካልታወቀ ብረት የተሠራ የብረት ሳህን በደረቷ ላይ ተጣብቋል፥ በእሳትም ፈጽሞ አይጠፋም ነበር። ሰሀኑ ላይ ግልጽ ባልሆነ ቋንቋ የተጻፈ "**በዚህ ያለሁት በዝሙት ነው**" የሚል ጽሑፍ አለ።

ጌታም ባያት ጊዜ ጠየቃት "***ኤለና፥ እዚህ ያለሽው ለምንድን ነው?***" ኤለና ለጌታ እየመለሰች ሳለ ሰውነቷ በስቃይ ህማም የተነሳ ተጠመዘዘ። ለጌታ በዚያ ያለችው በዝሙት እንደሆነ ነገረችው። ደጋግማም ይቅርታን ጠየቀችው።

ከዚያም ያሚሚቷን ሁኔታዎች ማየት ጀመርን። በሞተች ጊዜ አብሯት የሚኖረው ሰው ወደ ሌላ ቦታ የሄደ መስሏት ከአንዱ ፍቅረኛዋ ጋር ግንኙነት እያረገች ነበር። ነገር ግን ከሥራው ሲመለስ ከሌላ ሰው ጋር  አልጋ ውስጥ አገኛት። ወደ ማድቤት ሄዶ ትልቅ ቢላ አመጣና ጀርባዋ ላይ ሰካው ከዚያም ወደ ሲያል ወረደች፥ ልክ ስትሞት እንደ ነበረችው። ራቁቷን።

በሲያል ሁሉም ነገር እውነታ ሆኖ ያ ቢላ በጀርባዋ ውስጥ አለ፥ ከባድ ህመምም ይፈጥርባታል። በዚህ ወቅት፣ በሲያል 7 ዓመት ሆኗት ነበር እናም ግን እያንዳንዷን የህይወቷንና የሞቷን ቅጽበት ታስታውሳለች። እንዲሁም ደግሞ ስለ ኢየሱስ ሊሰብካት የነበረን አንድ ሰው ታስታውሳለች፥ ሊያድናት የነበረው ብቸኛው ሰው እርሱ ነበር። አሁን ግን ለእርሷም ሆነ በሲያል ላሉት በጣም ረፍዷል።

የጌታ ቃል ስለዝሙት ብዙ ያወራል፥ እናም በጣም ግልጽ ነው። ዝሙት ከትዳር ውጪ ያታዊ ግንኙነት ማድረግ ነው። [1ቆሮንጦስ 6:13] "***መብል ለሆድ ነው፥ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሥጋ ነው።***" እንደገናም [1ቆሮንጦስ 6:18] "***ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።***"

ጌታም አነጋግሯት በጨረሰ ጊዜ ትልቅ የእሳት ብርድልብስ ሸፈናት፥ እኛም ከዚያ በኋል ልናያት አልቻልንም። ሰውነቷ ሲቃጠል ያለው ድምጽ እንዲሁም አሰቃቂ ጩኸቷ ይሰማን ነበር፥ በቃላት እንኳን ልገልጻቸው አልችልም።

ከጌታ ጋር እየሄድን ባለንበት ጊዜ ብዙ ዓይነት ሰዎችን አሳየን፤ ጣዖት አምላኪውን፣ ጥንቆላን ያዘወትሩ የነበሩ፣ ዘማዎች፣ ውሸታሞች፣ ግብረሰዶማውያን። በጣም ፈርተን ነበር፥ ከዚያ ቦታ መውጣት ብቻ ነበር የምንፈልገው። ነገር ግን ጌታ ሌሎች እንዲያምኑ እንነግራቸው ዘንድ ማየት እንደሚያስፈልገን ይነግረን ነበር።

የጌታን እጅ የበለጠ አጥብቀን ይዘን መሄድ ቀጠልን። በእኔ ላይ የምር ተጽእኖ ያደረገብኝ ክፍል ደረስን። 23 ዓመቱ የሆነ ወጣት በወገብ ከፍታ በእሳቱ መኻል ተንጠልጥሎ አየን። ስቃዩ ምን እንደሆነ በግልጽ ማየት አልቻልንም፥ ነገር ግን 666 የሚለው ቁጥር ታትሞበት ነበር። እንዲሁም ደግሞ በደረቱ ላይ እንዲህ የሚል የብረት ሳህን አለ "**እዚህ ያለሁት ተራ ሰው በመሆኔ ነው።**" ኢየሱስን ባየው ጊዜ፥ ምህረትን እየለመነ እጁን ወደ ኢየሱስ አስረዘመ። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል [ምሳሌ 14:12] "***ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።***"

"**እዚህ ያለሁት ተራ ሰው በመሆኔ ነው።**" የሚለውን ጽሑፍ በደረቱ ላይ ባየን ጊዜ ጌታን ጠየቅነው፥ "*ጌታ ሆይ፥ እንዴት!? ሰው በዚህ ምክንያት ወደ እዚህ ቦታ ሊመጣ ይችላል?*" ከዛ ጌታ ጠየቀው "***አንድሪው፥ ለወምንድን ነው በዚህ ቦታ ያለኸው?***" እርሱም መለሰ "*ጌታ ሆይ፥ በምድር ላይ ሳለሁ፥ መግደልና መስረቅ ብቻ ነበር ኃጢአት የሚመስለኝ፥ ለዛ ነው ወደ አንተ ለመቅረብ በፍጹም ያልሞከርኹት።*" በ[መዝሙር 9:17] እንዲህ ይላል "***ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ፥ እግዚአብሔርን የሚረሱ አሕዛብም ሁሉ።***"

አንድሪው አሁንም ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት ኃጥያትን በመከፋፈሉ ትልቅ ስህተት ሰርቷል። መጽሐፍ የኃጥያት ደሞዙ ሞት ነው፥የእግዚአብሔር ስጦታ ግን የዘላለም ህይወት ነው (ሮሜ 6፡23) ሲል በጣም ግልጽ ነው። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ኃጥያትን ሲገልጸው አልከፋፈለውም፥ምክንያቱም ኃጥያት ኃጥያት ነው፡፡ አንድሪው ኢየሱስን የማወቅና የመቀበል አጋጣሚ ነበረው ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠውን እድሉን አልተጠቀመበትም። ምናልባት ጌታን የማወቅ ሺህ እድል ነበረው፥ ነገር ግን በጭራሽ ሊያውቀው አልፈለገም፥ ለዚህም ነው በሲያል ያለው። ከዛም ትልቅ የእሳት ብርድልብስ መጥቶ ሸፈነው ከዚያ በኋላ ድጋሚ አላየነውም።



ከጌታ ጋር መሄዳችንን ቀጠልን። በርቀት የሆነ ነገር ሲወድቅ አየን፥ ልክ እንደ ብዙ እቃዎች። በተጠጋን ጊዜ በዚያን ሠዓት ወደ ሲያል የሚወድቁ ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስ ክርስቶስን በልባቸው ሳይቀበሉ የሞቱ ነፍሳት ነበሩ ወደ ሲያል እየወደቁ የነበሩት።
የሆነ ወጣት ሰው አየን፥ ጋኔሎቹ ወደ እርሱ እየሮጡ ሄዱና ሰውነቱን ማውደም ጀመሩ። ወዲያውኑ ሰውነቱ በትሎች መሞላት ጀመረ። ጮኸ "አይሆንም! ምንድር ነው? እዚህ ቦታ መሆን አልፈልግም! አቁሙ! ህልም መሆን አለበት! *ከዚህ ቦታ አውጡኝ!* " መሞቱንም አላወቀም ነበር፥ክርስቶስ በልቡ ሳይኖር መሞቱን። ጋኔኖቹም እያሾፉበትና ሁል ጊዜም ሰውነቱን እያሰቃዩት ነበር።ከዚያም በግንባሩ ላይ 666 የሚለው ቁጥር፥ በደረቱ ላይ የብረት ሳህን ወጣ። ምንም እንኳን ወደ ሲያል የመጣበትን:ምክንያት:

ማየት ባንችልም በእርግጠኝነት ግን ተመልሶ መውጣት እንደማይችል አውቀናል።

ጌታም የእነዚህ ሰዎች ስቃይ በፍርድ ቀን የባሰ እንደሚጠነክር ነገረን። አሁን እንደዚህ ባለ አስከፊና ዘግናኝ ሁኔታ የሚሰቃዩ ከሆነ ከፍርድ ቀን በኋላ ምን ያህል እንደሚሰቃዩ ማሰብ ይከብደኛል።

ምንም ልጆች አላየንም። ሺሆችና ሺሆች ወጣቶች እንጂ፥ ወንዶችና ሴቶች የሆኑ የተለያዩ ሕዝቦች። በሲያል ውስጥ በጭራሽ ብሔርና የኑሮ ደረጃ የለም፥ ሁሉም የሚመጡት ሊሰቃዩና ለቅጣት ነው። ሁሉም ሰው የሚፈልገው አንድ ነገር አለ ቢያንስ ለአንድ ሰከንድ እንኳን ከዚያ መውጣት። እንዲሁም ምላሳቸውን ለማርካት አንድ ጠብታ ውኃ፥ልክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው እንደ ሀብታሙ ሰው ታሪክ። (ሉቃስ 16፡19) ነገር ግን ከአሁን በኋላ ይህ አይቻልም፥ ለዘላለም የሚያሳልፉበትን ቦታ ሊመርጡ። ከእግዚአብሔር ውጭ ለማሳለፍ ወስነዋል። እግዚአብሔር ማንንም ወደ ሲያል አይልክም፥ ሁሉም እንደየ ሥራው ይገባል። ገላትያ 6:7 "*አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና።*"

ዛሬ ዘላለማዊ እጣ ፋንታችሁን ለመቀየር ታላቅ እድል አላችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም ይገኛል፥እናም መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወት ሳለን ተስፋ እንዳለን ይነግረናል። ዛሬ ሕይወት አላችሁ፥ ይህ እድል እንዳያመልጣችሁ፥ምን አልባትም የመጨረሻችሁ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, matoughen@gmail.com